ሀሳበ ባሕር (የዘመን ቁጥር)

ጊዜን መቁጠር ዘመንን መስፈር የተጀመረው ከሥነ ፍጥረት ጀምሮ ነው፤ እግዚአብሔር አምላክ አዳምንና ሄዋንን ፈጥሮ በነፍስ ሕያዋን አድርጎ በመንፈስ ቅዱስ አክብሮ ከአንዲት እፀ በለስ በቀር ከፀሐይ በታች ከምድር በላይ ባለው ሁሉ ላይ አሰልጥኖ (ሾሞ) በገነት አኖራቸው። ሁለቱ የመጀመሪያ ሰዎች ያለምንም ችግር ሕጉን ጠብቀው ትእዛዙን አክብረው ለሰባት ዓመት በገነተ ኖረዋል። " በመጀመሪያው ሱባኤ፣ በመጀመሪያው ኢዮቤልዩ አዳምና ሚስቱ በገነት " ኖሩ ይላል። ኩፋ 4÷14 ከዚህ በኋላ አዳም በጠላት ዲያብሎስ ክፉ ምክር ተታሎ ሕጉን ጥሶ፣ ትእዛዙን አፍርሶ ከተሳሳተ በኋላ ከገነት ተባረረ። እግዚአብሔርም በዚያው እንደተባረረ እንዲቀር ስላልፈለገ በ5500 ዘመን ሰው ሆኜ አድንህለሁ ወደ ቀደመ ክብርህ እመልስሃለሁ ብሎ ተስፋ ሰጠው። አዳምም ይህን ተስፋውን ይዞ ለልጆቹ ፣ልጆቹም ለልጅልጆቻቸው ነገሩአቸው ። እነሱም ከአባቶቻቸው ተቀብለው እኩሎቹ በፀሐይ፣ እኩሎቹ በጨረቃ፣ ሌሎቹም በከዋክብት እየቆጠሩ መኖር ጀመሩ። በዚህ ሁኔታ የዘመን አቆጣጠር ታሪክ ተጀመረ።

የዘመን አቆጣጠር ታሪክ መነሻ የ5500 ዘመን መፈጸምን ለመድረስ የሚደረግ ወደ ታች የሚቆጠር ሂደት ነበር። ከአዳም ጀምሮ በዚህ ሁኔታ ቢነሳም በዚሁ አልቀጠለም;። ምክንያቱም የሰው ዘር በምድር ላይ እየበዛ በሄደ ቁጥር ለቀን፣ መቁጠሪያ ለዘመን መስፈሪያ፣ ለሰው ልጅች መገልገያ ሊሆኑ የተፈጠሩ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብትን የሰው ልጆች አምላካቸው አድርገው አመለኳቸው። ነገር ግን ተስፋቸውን ያልረሱ ጥቂት ሕዝቦች ብቻ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ቀሩ።

ስለሆነም የዘምን አቆጣጠር በልዩ ልዩ ሕዝቦች በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ አካሄዶችን በመከተል ሲሰራበት ኖሯል። በመሆኑም ከአዳም እስከ ልደተ ክርስቶስ ያለውን የዘመን አቆጣጠር ከብዙ በጥቂቱ እንደሚከተለው እናቀርባለን።

1. **ሱባዔ አዳም፡-**

አዳም በገነት ሰባት ዓመት ከአንድ ወር ከአስራ ሰባት ቀን በደስታ ከኖረ በኋላ ምክረ ከይሲን ሰምቶ እፀ በለስን በልቶ ከገነት ወጣ። ከዚህ በኋላ 35 ቀን ሱባዔ ገብቶ ተጨማሪ 3 + 3 = 6 ቀን በመንገድ ቆይቶ ከ 41 ቀን በኋላ ተስፋ ተሰጠው።

2. **ሀሳበ ሔኖክ** ፡-

ሄኖክ በቤተክርስቲያንም ሆነ በዓለም ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን መፅሐፍ የጻፈ እሱ ነው፡፡ በሐሳበ ሄኖክ መስፈርት መሠረት 35 ዓመት እንደመሥፈርት ይቆጠራል፡፡ በሌላ አካሄድ ደግሞ ሰባ መቶ ዓመትን እንደ አንድ መሥፈርት ይቆጥራል፡፡ በዚህም መሠረት 35ቱ ዓመት እንደ አንድ ሆኖ በ19 ሲባዛ 665 ዓመት ይሆናል፡፡ ይህ 12 × 665 = 7980 ዓመት ይሆናል፡፡ ይህም ምፅአቱን የዓለምን ፍፃሜ ያመለክተናል፡፡ ነገር ግን ምፅአቱን የዓለምን ፍፃሜ ከባለቤቱ በቀር የሚያውቅ የለም ፡፡(ማቴ 24÷36)

3. <u>ኢዮቤልዩ ዘሙሴ</u>፡-

ሙሴ ሕግን ከእግዚአብሔር የተቀበለ ያኑ ሕግ ለእስራኤል ያስተላለፈ ያስተማረ ነቢይ ነው ፡፡ አያይዞም ትንቢት ተናሯል ፣ ሱባዔ ቆጥሯል፡፡ የሙሴ አቆጣጠር በኢዮቤልዩ ነው፡፡ የእርሱ ኢዮቤልዩም ሦስት ነው፡፡ ሦስቱን እስከ አስራዘጠኝ ቢወስዱት 3 ሲባዛ በ19 = 57 ይሆናል ፡፡ ይህም እስከ 140 ይሄዳል፡፡ 140 × 57 =7980 ይሆናል፡፡

4. **ቀመረ ዳዊት**፡-

ልበ አምላክ ዳዊት ነቢይም ነው፡፡ ምክንያቱም የአምላክ ሰው መሆን ተገልጦለት እነሆ በጨርቅ ተጠቅሎ በጎል ተጥሎ በግዕዘ ሕፃናት ሲያለቅስ ሰማነው ብሎ ተናግሯልና መዝ 131÷5 ልበ አምላክ ዳዊት ከእርሱ በፊት እንደነበሩት ነቢያት ሱባዔም ቆጥሯል፡፡ “ሺህ ዓመት በፊትህ እንዳለፈች እንደ ትናንት ቀን ናት ” ብሎ መዝ 89÷4 ይህም ዘመን ሲቆጠር 1140 ዓመት ይሆናል፡፡ ታዲያ ልበ አምላክ ዳዊት ይህን 1140 ዘመን በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ አንድ እለት ነው ብሎ ተናገረ በቀመረ ዳዊት መሠረት ይህ 1140 ዓመት የዘመን መስፈሪያ የቀን መቁጠሪያ ነው፡፡ 1140ውን ዓመት እስከ ሰባት ቢወስዱት 7 ×1140= 7980 ዓመት ይሆናል፡፡ እስከዚህ ድረስ ያለው ከአዳም እስከ ልደተ ክርስቶስ የነበሩ ነቢያት ከቀመሩት ቀመር ለመግቢያ ያህል የተወሰነውን ሲሆን በመቀጠል ግን በሐዲስ ኪዳን በ3ኛው መቶ ክ/ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ሊቁ የእስክንድርያው ሊቀጳጳስ ዲሜጥሮስ የደረሰውን ባሕረ ሀሳብ በተለይም በ2006 ዓ.ም በዘመነ ማርቆስ የሚውሉ በዓላትና አፅዋማትን ጨምሮ ተዘጋጅቷል፡፡

በሐዲስ ኪዳን

ስለዘመን አቆጣጠር የጻፉና ያስተማሩ ብዙ ሊቃውንት አሉ፡፡ ከነዚህ ሊቃውንት መካከል የእስክንድርያው ሊቀጳጳስ ዲሜጥሮስ አንዱ ነው ነው፡፡ የመጀመሪያውን

የዘመን አቆጣጠር ከሐዲስ ኪዳን በዓላት እና አዕዋማት ጋር አስማምቶ የመሠረተ እና ባሕረ ሐሳብ የተባለውን መጽሐፍ የደረሰውም ይኸው ቅዱስ ዲመጥሮስ ነው።።

ባሕረ ሀሳብ ማለት በውስጡ እንደ ባሕር ጥልቀት ያላቸው ጉዳዮች ያሉበት የዘመን ቁጥር ማለት ነው።። ስለዚህ ባሕረ ሀሳብ ሲባል የዓመታት፣ የወሮች ፣ የሳምንታት፣ የዕለታትና፣ የደቂቃዎች ልክ የሚታወቅበት የዘመን መቁጠሪያ ፣ መሥፈሪያ ማለት ነው።። መርሐ እውርም ይባላል።። በዓላትና አዕዋማት የሚውለብትን ዕለት ወደ ማወቅ መርቶ ያደርሳልና።።

ዲሜጥሮስ ማለት መስታወት ማለት ነው።፤ በመስታወት በዓይን ያለ ጉድፍ እንዲታይ እሱም በዓላት አዕዋማትን አጉልቶ አምልቶ ያሳያልና።።

ይህም ቅዱስ ዲሜጥሮስ ድግ ታጥቆ እርፍ አርቆ ተክል አጽድቆ ይኖር የነበረ ገበሬ ነበር።። ሚስቱም ልዕልተ- ወይን ትባላለች።። እናት አባቷ ሙተውባት ከእርሱ ቤተሰቦች ጋር ያደገች ናት።። ነገር ግን እርሱም እሷም ሳይፈልጉ አጋብተዋቸዋል።። እናት አባቱም ያጎቱን ልጅ ማጋባታቸው ዘመኑ ምእመናን ያነሱበት አሕዛብ የበዙበት ዘመን ነበርና ለርሱ የምትሆን ሚስት በመታጣቷ ሕንፃ ሃይማኖት ከሚፈርስ ሕንፃ ሥጋ ይፍረስ ብለው ዝምድና እያላቸው አጋብተው ሥርዓተ መርዓዊና መርዓት ያድርሱ ብለው ከጫጉላ አስገቡአቸው ነገር ግን ልዕልተ ወይን ወንድሜ አንተም ነግሩን ሸተኸው ነው? አለችው እርሱም የግድ ቢሉኝ ጊዜ ነው እንጂ ነግሩንስ እንዳልሸው እግዚአብሔር ያውቃል።። አሁንም የተለያየን እንደሆነ አንችንም እኔንም ለሌላ ያጋቡናልና በአንድ ላይ ንፅሕ ጠብቀን መኖር እንችላል ተባብለው በአንድ አልጋ እየተኙ አንድ ልብስ እየለበሱ 48 ዘመን በንፅሕና ኑረዋል።። ይኸውም እንዲታወቅ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ግራ ክንፉን ለሷ ቀኝ ክንፉን ለሱ አልብሷቸው ያድር ነበር።።

ከዕለታት በአንድ ቀን ቅዱስ ዲሜጥሮስ ከአትክልት ቦታ ገብቶ ያለጊዜው ያፈራ የወይን ዘለላ አግኝቶ ወሰዶ ለልዕልተ ወይን ሰጣት እርሷም ይህንስ ወስደህ ለሊቀጳጳሱ ስጥተህ በረከት ተቀበልበት ብላ በንፁሕ ሙዳይ አድርጋ ሰጠችው።። በዘመኑ የነበረው የእስክንድርያው ሊቀጳጳስ ዮልያኖስ ይባል ነበር ።። አርጅቶ የሚሞትበት ጊዜ ቀርቦ ነበርና መልአኩ ከአንተ ቀጥሎ የሚሾመው ያለጊዜው ያፈራ የወይን ዘለላ ያዞ የሚመጣ ሰው ነው ብሎ ነግሮት ስለነበረ ዲሜጥሮስ አምጥቶ ሲሰጠው ሕዝቡን ሰብስቦ ከኔ ቀጥሎ የሚሾመው እርሱ ነው ብሎ ነግሮአቸው አርፎአል

ሕዝቡም እሱን ቀብረው ተመልሰው አባታችን ከኔ ቀጥሎ የሚሾመው እርሱ ነው ብሎናልና ተሾምልን አሉት።

እርሱም ተሹሞ ብዙ መንፈሳዊ ሥራዎችን ከመሥራቱ በተጨማሪ የሕዝቡ ኃጢአት እየተገለፀለት አንተ በቅተሃል ቀረብ አንተ ልበቃህም አትቀረብ እያለ የሚከለክላቸው ሆነ። ሕዝቡም ተቆጥተው ያጉረመርሙ ጀመር። በዚህ ጊዜ መልአኩ ተገልጦ ሕዝቡ በሃሜት እየተጎዱ ነውና በአንተና በሚስትህ መሀከል ያለውን ነገር ግለፅላቸው አለው። እሳት አስነድዶ ሚስቱን ከመቅዋመ አንስ አስጠርቶ ፍሙን በእጁ እየዘገነ (እያፉሰ) ወደ ሚስቱ ልብስ እየጨመረ ሄደሽ ለሕዝቡ አሣይ አላት እሷም ፍሙን (እሳቱን) በልብሷ ይዛ እሳቱ ልብሷን እየዞረች ለሕዝቡ አሣይታለች። ከዚህ በኋላ ሕዝቡ አባታችን በከንቱ አምተንሃልና ይቅር በለን አሉት። እርሱም ይፍታሕ፣ ይጎድግ፣ ያንፅሕ ወይቀድስ ብሎ ናዝዞአቸዋል ኑዛዜ የተጀመረው ከዚያ ወዲህ ነው።

የቀድሞ ሰዎች አቢይ ጾምን የጥምቀት ማግሥት ይጀምሩ ነበር። ሕማማቱንም አዘግይተው (አቆይተው) በመጋቢት ያደርጉ ነበር። በዚህ የተነሳ የዓቢይ ጾም የጥምቀትን ሳኒታ መነሻ አድርጎ ስለሚጀመር ሰኞን ፣ ደብረ ዘይት፣ ሆሣዕና፣ ትንሣኤ፣ ጸራቅሊጦስ እሁድን ሳይጠብቁ ይውሉ ነበር።

በዚህም ቅዱስ ዲሜጥሮስ፡-

- ጾመ ነነዌ፣ ዓቢይም ጾመ ሐዋርያት..... ከሰኞ
- ደብረ ዘይት፣ ሆሣዕና፣ ትንሣኤ፣ ጸራቅሊጦስ.....ከእሁድ
- ርክበ ካህና፣ ጾመ ድህነት..... ከረቡዕ
- ስቅለት..... ከዓርብ
- ዕርገት..... ከሐሙስ

ባይወጡ? እያለ ሲመኝ ይኖር ነበር። መልአኩ ተገልጦ ነገር በማሰብ ብቻ ይሆናልን ሱባዔ ገብተህ ይገለፅልሃል አለው። ሱባዔ በገባ ጊዜ መላኩ መጥቶ ከመአልቱ ሰባት ሱባዔ ከሌሊቱ ሃያ ሦስት ሱባዔ ገብተህ ይገለጽልሃል። ይህን በ30 በ30 ገድፍህ በተረፈው ታገኘዋለህ ብሎታል። በዚህም መሠረት የመዓልቱ 7 × 7= 49 ይህ በ30 ሲገድፉ 49-30= 19 ይቀራል። ይህ 19 የጥንተ መጥምቅ ተባለ። የሌሊቱ 23ቱን አንድ እያለ 7 ጊዜ ይሰገድ ነበር። 23 × 7 = 161 ይን 161 በአምስት 30 ብንገድፈው 161-5 × 30 = 11 ይተርፋል ይህን አበቅቴ ብለው ብሎታል ይህን ቢደምሩት 30 ይሆናል። ይህን አዘጋጅቶ ጽፎ ለ4ቱ

ሊቃነጳጳሳት ቢልክላቸው እነሱም ቀድሞ ሐዋርያት ካስተማሩት ትምህርት ጋር ስለገጠመላቸው ደስ ብሏቸው ተቀብለውታል።

- መጥቅዕ ቢያንስ አበቅት ቢበዛ አበቅቴ ቢያስ መጥቅዕ ቢበዛ ከ30 አይበልጥም ከ30 አያንስም።

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ አሁን እስከአለንበት ቢቆጠር 7506 ዓ.ዓ ይሆናል። ለዚህም መቁጠሪያ ፣ መሥፈሪያ ሰባት አእዋዳ አሉት።

እነዚህም

ዐውደ ዕለት

ዐውደ ወርኀ

ዐውደ አበቅቴ

ዐውደ ዓመት

ዐውደ ፀሐይ

አውደ ማኅተም

አውደ ቀመር

የዘመኑን መጥቅዕና አበቅቴ ለማወቅ አመተ ዓለሙን ለአብይ ቀመር (532) መሥጠት ነው።

7506 ÷ 532 = 14 ቀሪ 58

ቀሪውን በሦስት ንዑስ ቀመር (19) መጣል። (19) 58 ÷ 19 = 3 ቀሪ 1

ይህ መደብ ይባላል።

አሐደ አእትት ለዘመን ብሎ አንድ ቢቀንሱ አልቦ (0) ይሆናል

አልቦ ወንበር አልቦ አበቅቴ ይባላል።

- አበቅቴ አንድ አይወጣም
- መጥቅዕ 29 አይወጣም
- "አንድ አበቅቴ 29 መጥቅዕ የሚያወጣ የተወገዘ ነው"። (አቡሻኽር) በአልቦ አበቅቴ ጊዜ መጥቅዕ 30 ይሆናል። በመጥቅዕ ሥርዓት መሠረት መጥቅዕ ከ14 በላይ ከሆነ በዓለ መጥቅዕ መስከረም ላይ ስለሚውል ነነዌ በጥር ትውላለች። በአልቦ አበቅቴ ጊዜ ግን ይህ አይሰራም መጥቅዕ 30 ስለሚሆን ነነዌ ከየካቲት ላይ ትውላለች። በዚህ መሠረት በ2006 ዓ.ም በዘመነ ማርቆስ ነነዌ በየካቲት ትውላለች ማለት ነው።

መባጃ ሐመርን ለማግኘት መጥቅዕና በዐለ መጥዕቅ የዋለበት ዕለት ተውሳክ ተደምሮ የሚገኘው ቁጥር መባጀ ሐመር ይባላል፡፡

በዚህም መሠረት መባጃ ሐመር = መጥቅዕ + በዐለ መጥቅዕ የዋለበበት ተውሳክ፡፡

መጥቅዕ ቢበዛ ከመስከረም ንዛ መጥቅዕ ቢያንስ ጥቅምትን ዳስ እንዲለ መጥቅዕ ሲበዛ በዓለ መጥቅዕ መስከረም ላይ ይውላል፡፡ መጥቅዕ ቢያንስ በዓለ መጥቅዕ ጥቅምት ላይ ይውላል፡፡ መጥቅዕ በዛ የሚባለው ከ14- በላይ ሲሆን ነው፡፡ አነሰ የሚባለው ደግሞ ከ14 በታች ሲሆን ነው፡፡ በዚህም መሠረት የ2006 ዓ.ም በዘመነ ማርቆስ መጥቅዕ 30 ከ14 በላይ ስለሆነ መስከረም 30 ላይ ሐሙስ ቀን ይውላል፡፡

መባጃ ሐመር = መጥቅዕ + መጥቅዕ የዋለበት ዕለት ተውሳክ፡፡

የሐሙስ ተውሳክ ሦስት ነው መጥቅዕ 30 + የሐሙስ ተውሳክ 3 = 33

33 - 30= 3 መባጃ ሐመር ወጣ በ2006 ዓ.ም በዘመነ ማርቆስ

የመባጀ ሐመር አገልግሎት የሚሰጡው ከበዓላትና አፅዋማት ተውሳክ ጋር እየተደመረ በዓላት አፅዋማትን ማስገኘት ነው፡፡

ከጾመ ነነዌ ውጪ ያሉ አጽዋማትና በዓላት ሁሉም ተውሳክ አላቸው ጾመ ነነዌ ግን ተውሳክ የለውም የሚያገኘው (የሚወጣው) በመባጀ ሐመር ነው፡፡ መጥቅዕ ከዕለት ተውሳክ ጋር ተደምሮ ከ30 ከበለጠ ጾመ ነነዌ በየካቲት ትውላለች ብለናል፡፡ በመሆኑም የ2006 ዓ.ም መጥቅዕ 30 + የዕለተ ተውሳክ 3 = 33

33 — 30 = 3 መባጀ ሐመር ወጣ በ2006 ዓ/ም በዘመነ ማርቆስ

በዓለ መጥቅዕ ከመስከረም ላይ ሲውል ጾመ ነነዌ በጥር በዓለ መጥቅዕ ከጥቅምት ላይ ሲውል ጾመ ነነዌ በየካቲት ይውላል፡፡

በመሆኑም በ2006 ዓ.ም ጾመ ነነዌን ለማግኘት 3 መባጀ ሐመር + 30 መጥቅዕ ተደምሮ ከ30 በላይ በመሆኑ ጾመ ነነዌ በየካቲት ነው የሚውለው በ2006 ዓ.ም በዘመነ ማርቆስ የካቲት በጥቅምት ማግስት (ሳኒታ) ቅዳሜ ይብታል፡፡

ቅዳሜ1፣ እሁድ2፣ ሰኞ 3 የካቲት በባተ በ3 (የካቲት 3 ቀን) ጾመ ነነዌ ይውላል።

የአጽዋማት እና በዓላት ተውሳክ

አፅዋማትና በዓላት	ተውሳክ
የዐቢይ ጾም	14
የደብረ ዘይት	11
የሆሣዕና	2
የስቅለት	7
የትንሣኤ	9
የርክበ ካህናት	3
የዕርገት	18
የጰራቅሊጦስ	28
የጾመ ሐዋርያት	29
የጾመ ድኅነት	1

ዐቢይጾም፡-

በ2006 ዓ.ም ዐቢይ ጾም የሚውልበትን ዕለት ለማግኘት የዐቢይ ጾም ተውሳክ 14 + መባጀ ሐመር 3 = 17 የካቲት በባተ (በገባ) በ17 ዐቢይ ጾም ይውላል።

ደብረ ዘይት፡-

በ2006 ዓ.ም ደብረ ዘይት የሚውልበትን ዕለት ለማግኘት የደብረ ዘይት ተውሳክ 11 + መባጀ ሐመር3 = 14 መጋቢት በባተ በ 14 (መጋቢት 14 ቀን) ደብረ ዘይት ይውላል።

ሆሣዕና፡-

በ2006 ዓ.ም ሆሣዕና የሚውልበትን ዕለት ለማኘት የሆሣዕና ተውሳክ 2 + 3 = 5 ሚያዝያ በባተ በ5 (ሚያዝያ 5 ቀን) ሆሣዕና ይውላል።

ስቅለት፡-

በ2006 ዓ.ም ስቅለት የሚውልበትን ዕለት ለማግኘት የስቅለት ተውሳክ 7 + 3 መባጀ ሐመር = 10 ሚያዝያ በባተ በ10 (ሚያዝያ 10 ቀን) ስቅለት ይውላል፡፡

ትንሣኤ፡-

በ2006 ዓ.ም የትንሣኤ ተውሳክ 9 + 3, 12 ሚያዝያ በባተ በ12 (ሚያዝያ 12) ትንሣኤ ይውላል፡፡

ርክበ ካህናት ፡-

በ2006 ዓ.ም ርክበ ካህናት የሚውልበትን ዕለት ለማግኘት (ለማወቅ) የርክበ ካህናት ተውሳክ 3 +3 መባጀ ሐመር = 6 ግንቦት በባተ በ6 (ግንቦት 6 ቀን) ርክበ ካህናት ይውላል፡፡

ዕርገት፡-

በ2006 ዓ.ም ዕርገት የሚውልበትን ዕለት ለማግኘት (ለማወቅ) የዕርገት ተውሳክ 18 +3 መባጀ ሐመር = 21

ግንቦት በባተ በ21 (ግንቦት 21 ቀን) ዕርገት ይውላል፡፡

ጰራቅሊጦስ፡-

በ2006 ዓ.ም ጰራቅሊጦስ የሚውልበትን ዕለት ለማግኘት (ለማወቅ) የጰራቅሊጦስ ተውሳክ 28 + 3 መባጀ ሐመር = 31-30 = 1

የሰኔ መባቻ (ሰኔ 1 ቀን) ጰራቅሊጦስ ይውላል፡፡

ጸመ ሐዋርያት፡-

በ2006 ጸመ ሐዋርያት የሚውልበትን ዕለት ለማግኘት (ለማወቅ) የጸመ ሐዋርያት ተውሳክ 29 +3 መባጀ ሐመር = 32 -30 = 2 ሰኔ በባተ በ2

ሰኔ 2 ቀን ጸመ ሐዋርያት ይውላል፡፡

ጸመ ድኅነት ፡-

በ2006 ዓ፣ም ጸመ ድኅነት የሚወልበትን ዕለት ለማግኘት የፆመ ድኅነት ተውሳክ 1 + 3 መባጀ ሐመር = 4

በ4 (ሰኔ 4 ቀን) ጸመድኅነት ይውላል፡፡

በ2006 ዓ.ም በዘመነ ማርቆስ የሚውሉ በዓላት አፅዋማትና የሚውሉባቸው ዕለቶች

ጾመ ነቢያት..... ሕዳር 15

ጾመ ነነዌ ..... የካቲት 3

ዐቢይ ጾም ..... የካቲት 17

ደብረ ዘይት.....መጋቢት 14

ሆሣዕና..... ሚያዝያ 5

ስቅለት..... ሚያዝያ 10

ትንሣኤ ..... ሚያዝያ 12

ርክበ ካህናት ..... ግንቦት 6

ዕርገት ..... ግንቦት 21

ጰራቅሊጦስ..... ሰኔ 1

ጾመ ሐዋርያት..... ሰኔ 2

ጾመ ድኅነት..... ሰኔ 4

ጾመ ፍልሰታ ..... ነሐሴ 1

እነዚህ ከዚህ በላይ የቀረቡ በ2006 ዓ.ም በዘመነ ማርቆስ ያሉ በዓላት አጽዋማት የሚውሉባቸው ዕለታት ሲሆኑ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ያለ ማንኛውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ቀኖና ቤተክርስቲያንን ጠብቆ በዓላትን ለማክበር አፅዋማትን ለመጾም ይጠቅማል ብለን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር